*በሎስ አንጀለስ የቅንጅት የርዳታና ልማት ድርጅት*
***Kinijit's Los Angeles Support and Development Association for Democracy (KINIJIT)***
***5768 W. Pico Blvd., Suite No. 207, LA, CA 90019***
***E-mail*: kinijitla@kinijitla.org website www.kinijitla.org**

# የሎስ አንጀለስ ኢትዮጵያውያን መሪዎቻችንን ለማስፈታት ድምፃቸውን አሰሙ

በሎስ አንጀለስና በአካባቢው የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ዛሬ የካቲት 9 1999 ዓ.ም. (February16 2007) ከቅንጅት አለም አቀፍ የቀረበውን ጥሪ በመቀበል ታላቅ የተቃውሞ ሰልፍ አካሂደዋል።

ይህ ሰልፍ በኢትዮጵያ ውስጥ በግፍ ለሚሰቃዩት የፖለቲካ እስረኞች በተለይም የቅንጅት አመራርና የነፃው ሚዲያ አባላት እንዲሁም የሰብአዊ መብት ታጋዮች በመለስ በተመረጡ ዳኞች ሊፈረድባቸው የሚችለውን የትዕዛዝ ፍርድ በመቃወም ሆሊውድ በሚገኘው የሲኤንኤን (CNN) ዋና መስሪያ ቤት ፊት ለፊት በደመቀ ሁኔታ ተከናውኗል።

በርካታ ኢትዮጵያውያን በእስር ላይ የሚገኙትን ሃቀኛ የኢትዮጵያ መሪዎችን ፎቶግራፍ በመያዝ፣ የተለያዩ የወያኔ አምባገነናዊ አገዛዝን ለህዝብ የሚያሳውቁ የእንግሊዘኛ መፈክሮችን በማሳየት፣ የአሜሪካንና ኢትዮጵያን ባንዲራ ይዘው የወያኔን ኢዲሞክራሲያዊ አገዛዝ በማጋለጥ ጽሁፎችን በተለይም ለCNN ሰራተኞች በማደልና መፈክሮችንም በማሰማት አካባቢዉን አደምቀውት ውለዋል። ከሚነበቡት መፈክሮች መካከል "ዲሞክራሲ ለኢትዮጵያ"፣ "መሪዎቻችን ይፈቱ"፤ "የነፃው ፕሬስ አባላት ይፈቱ"፤ "CNN እውነቱን አጋልጥ" የሚሉ ይገኙበታል። በዚህ አጋጣሚም ለCNN የሎሰ አንጀለስ በሮ ከሎስ አንጀለስ ቅንጅት ድጋፍ ድርጅት የተጻፈ የኢትዮጵያን ወቅታዊ ሁኒታ የሚገልፅ እና የህዝቡን አቓም የሚያብራራ ፅሁፍ በተወካዮቻቸው አማካኝነት ተሰጥቶዋቻዋል። በተጨማሪም የሰልፉ ሂደት በሎሰ አንጀለስ KPFK 90.7 ራዲዮ ለአድማጮች በቀጥታ ተላልፏል።

ሰልፈኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሚያደርገው የሰላም ትግል አጋር መሆኑን እየገለፀ ለታሰሩት የፖለቲካ እስረኞችም አይዞአችሁ አለንላችሁ ከጎናችሁ ቆመናል ብለዋል።